EthioLion

# ስሙን ለሰው አወረሰው

እንዴት? ወይም ስለምን ብትሉኝ የማቀርብላችሁ መልስ በዝርዝር ይኸውላችሁ።
ሰሞኑን ከመገናኛ ብዙኃን እንዳያችሁትና እንደሰማችሁት የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ራሱን መለስ ባዩ ግን ለገሠ ዜናዊ የነበረው የአስተማሪዎችን ሥራ ማቆም፤ የኢኮኖሚውን ጠቅላላ ክስረትና የዋጋ ግሽበት፤የኑሮ ውድነት፤ የእስላም ኢትዮጵያውያን ጥያቄንና የብዙ ሺህ ያማራ ተወላጅ ገበሬዎች በዘር ፖለቲካ ባማራነታቸው ብቻ ተለይተው ለብዙ ዓመታት ከሚኖሩበት ቤታቸውና ንብረታቸው ከደቡብ ቤንቺ ጉራፈርዳ ወረዳ በወያኔ ጉጅሌ የጎሣ ማፅዳት የተቀነባበረ ዘመቻ መባረራቸውን አስመልክቶ ለኢሕአዴግ ፓርላማ ተብዬ የተለጣፉፊዎች ጥርቃሞ ስብስብ ያደረገውን ወቅታዊ ንግግር በማገናዘብ ነው።

ለአስተማሪዎች ተገቢ የመብት ጥያቄ የሰጠው መልስ <<የሙያ ብቃትና ችሎታ የሌላቸው ጥቂት የአዲስ አበባና የአማራ ክልል አስተማሪዎች ብቻ እንደሆኑና እነዚህም በውጭና በወስጥ ነውጥ አራማጆች ከሚነዱት በስተቀር 99.9 ከመቶ አስተማሪዎች በደሞዝ ጭማሪውና የደረጃ ማሻሻዛው ተስማምተዋል።>> ብሎ በሬው ሳም ወለድ አቀርቢል። ይህም በትክክል ስሙን ለሰው አወረሰው ነው። ሙያና ብቃት የለሹማ ራሱ መለሰና ምድረ የወያኔ ኢሕአዴግ ስብስብ ካድሬና የባንቱስታን የጎሳ አባቆሮ ጥርቃሞ አጃቢዎቹና ጀሌዎች መሆናቸውን ድፍን አገር የሚያውቀውና ፀሓይ የሞቀው ነገር ነው።
ስለሆነም ነው ዕውቅና ባለሙያ ያዲስ አበባ የኒቨርስቲ መምህራን ተባረው የትምህርቱ ጥራት ውሃ የበላው። የቴሌ፣ የአየር መንገድ፣ የአየር ኃይል ወዘተረፈ ባለሙያ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እየተለቀሙ ተባረው በጎሳ ታማኝ ካድሬዎች መተካታቸውን ከቶ ማነው የሚረሳው? የወጋ ቢረሳ የተወጋ መቼም አይረሳም።

## ማን ነው አሸባሪው?

መላውን ኅብረተስብ ዕለት በለት አሸባሪው፣ በተለይም ጋዜጠኛውን፣ ምሁሩን፣ ተማሪውን፣ ሠራተኛውን፣ ነጋዴውን፣ ገበሬውን፣ ወዘተረፈ ሰብአዊ መብት ረግጦ የሚበዘብዘው፣ ለሙን መሬት ለአረብ፣ ለሕንድ፣ ለቻይና፣ ለአውሮፓና አሜሪካ ከበርቴዎች በርካሽ የሚቸበችበው፣ በጎሳና ሃይማኖት ሕዝቡን በጎሳ ከፋፍሎ የሚያጋጨው ማን ሆነና?
ነባሩን የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት በመጤ ለመተካት የሚቃዠነው? ጉድ እኮ ነው! "መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም" ተብሎ ይቦተለካል። እረ ማን ለማታለል? የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን የወያኔን ይቅርና የዝንብን ጠንባራ በሩቅ ይለያል። ማንነቱንም በምርጭያ 97 ለዓለም ሕዝብ አሳይቷል።
የእስልምናን ሆነ የኦርቶዶክስ ክርስትና ምእመናን በቀጥታ ለመቆጣጠር ካድሬዎችን መልምሎና አስታጥቆ የሚንቀሳቀሰው የወያኔ ኢሕአዴግ ተብዬ ቅጥረኛ ፋሽስትዊ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት ነው። ያቶ መለሰ በሃይማኖት አክራሪነት ጨንበል፣ በአልቃይዳ ሽፋን የእስላሙን ማኅበረሰብ ተገቢ ጥያቄ ለማፈን፣ ለማስፈራራት ያደረገው ማወናበጃ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። ወያኔ ኢሕአዴግ የውጭ ኃያለን መንግሥታት ቅጥረኛ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ቁልፍ ስፍራና አካባቢ የሰላምና ደህንነት ጠንቅና ዋና አሸባሪ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅምና ሳእላዊነት የሸጠ፣ የጠላት ተባባሪ አሸከርና ተላላኪ ጉዳይ አሰፈፃሚ ነው።

## አንድም የተፈናቀለ ስፋሪ የለም!

ሌላው ዓይኔን ግንባር ያርገው ስለ ዐማራ ተወላጆች ተፈናቃዮች የተዘላበደው ጉዳይ በጣም ያስገርማል።
በአንድ በኩል እንበለ እፍረት አንድም የተፈናቀለ ሰፋሪ የለም ተባለ። በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ጉራፈርዳ ከምሥራቅ ጎጃም በመጡ ወደ 30 ሺህ የሚጠጉ ሕገ ወጥ ሰፋሪዎች ያለ አግባብ ደኑን መነጠሩ፣ የአካባቢውን አየር ንብረትና ሥነ ምኅዳር ያቃወሱ ወንጀለኞች ተደርገዋል። ቀደም ብሎ የደቡብ ክልል የወያኔ ተወካይ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ግን ከሰሜኑ በተለይም ከዐማራ ክልል የመጡ ሰፋሪዎችን ይዞታችሁን አስረክባችሁ ወደ አገራችሁ ተመለሱ የሚል ትዕዛዝ አስተላላፈ እንጅ ሰፋሪዎችን በደን ምንጠራና ማውደም አልወነጀለም። አስገራሚው ትርኢት አዛዥና ታዛዥ ሐርአምባና ቆቦ መሆናቸው ነው።
ነገር ግን እነዚህ ኅበዝ ገበሬዎች ከየትኛውም አካባቢ ይምጡ ማለትም ከደቡብ ጎጃም ይሁን ወይም ከሰሜን ጎንደር ወይም ከወሎ ወይም ከሸዋ ወይም ከየትኛውም አቅጣጭያ በማኅበራዊ ኑሮ አስገዳጅነት ተንቀሳቅሰው ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋራ ተግባብተው፤ ተባብረውና ተዋሕደው በኢትዮጵያዊነታቸው ጥረው ግረው ያመቻቹትን፣ ሕይወትና ንብረት መንግሥት ነኝ በሚል የወያኔ ጉጀሌ ፀረ ዐማራ ጥርቃሞ ቡድን በነመለሰ ዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፤ በረከት ስምዖንና ብጤዎቻቸው የተቀነባበረ የጎሳ ማፅዳት ዘመቻ ነው። የጉራፈርዳን ሰፋሪዎቹ በዐማራነት ብቻ ለይቶ ኢሰባዊ ድርጊት የተፈጸመበቻው በቀጥታ ከአዲስ አበባ መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም ነው ከወር በላይ አቤቱታ ሲያቀርቡ ምንም ምላሽ ያላገኙት። በብዛት በአንድ ላይ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገቡ፣ መጠጊያ በቤተ ክርሲትያን ግቢም እንኳ እንዳያገኙ፣ ሕዝብ እንዳያያቸውና እንዳይገናኙ የተደረገው።
እድሜ ለመኢአድና ለአሜሪካ ድምፅና ሌሎች የመገኛኛ አውታሮች የጎሣ ማጽዳት ሰለባዎች ሰቆቃ ተመዝግቦ አይተናል፣ ሰምተናል። ታዲያ! መለሰና ጀሌዎቹ ጩኸቴን ቀሙኝ እንዲሉ ስንት ወራት ሙሉ ለገበሬዎች ጩኸትና ዋይታ ጆሮ ዳባ ልብስ ብለው ከሰነበቱ በኋላ አረመኔ ድርጊታቸው ተሸፋፍኖና ተሰውሮ ባለመቅረቱ ያማራ ክልል ተብዬው የወያኔ ወኪሎች ሰፋሪዎችን ከመኢአድ ጽ.ቤት አፍሰው በመውሰድና በመከፋፈል ከፊሉን ያለፈቃዳቸው ወደ ድብረ ብርሃን መላካቸውና ከደቡብም በጉዙ ላይ ያሉት ወደ አዲስ አበባ እንዳይገቡ ማድረጋቸው እየታወቀ ወያኔዎች ዐይናቸውን በጨው አጥበው አንድም ሰው አልተፈናቀለም እያሉ ይቀላምዳሉ።
በዐማራው ሕዝብ ላይ የሚያደርጉትን ጥቃትና ዘመቻ የተፈናቀለት 33 ደን መንጣሪዎች ብቻ ናቸው ወዘተረፈ እያሉ ከ78 ሺህ ሕዝብ በላይ ከቤት ንብረቱ ማፈነቀላቸውን ለመሸፈጥ በከንቱ አዳክረዋል። 1
ኢትዮጵያዊነት የጎን ውጋት ሆኖበት ሕሊናውን የሳተውኖ የሚያናውዘው የፋሽስት ዱቼ ሙሶሊኒ ሙት መንፈስ አድሮበት የሚቅበዘበዘው የባንዳው ውላጅ መለሰ ዜናዊ ከጉራፈርዳ ወረዳ የተፈናቀሉ ያማራ ገበሬዎችን በአዲስ አበባ ከተማ የረዱትን ድርጅቶችና ግለሰቦች "መንደረተኞች" እያለ ተሳድቧል፤ አስፈራርቷል።
እባቡ መለሰ ኩኩ መለኮቴ ሆኖ
<< በምሥራቅ ጎጃም የተቃጣ፣ በጉራፈርዳ የተቃጣ፣ ምሥራቅ ጎጃም ተደበደበ፣ ዐማራ ተጠረገ... የሚል ሃላፊነት የጎደለው ነገር ኢትዮጵያዊነትን መፈክራቸው ያደረጉት መንደረተኞች ናቸው>> እያለ ያማራ ጥላቻውን አቀርሽቷል።
ትርኢቱ ጩኸቴን ቀሙኝ እንዲሉ የወያኔ የጎሣ ፖለቲካ ዕቅድና ተግባራዊነት ሰለባ የሆኑት ያማራ አርሶ አደሮች ለምን በተለይም መጠጊያ አገኙ፣ የተፈጸመባቸው ኢሰባዊ ድርጊት፣ ሰቆቃና እንግልት ለምን በዓለም ዙሪያ ታወቀ፣ ታየ፣ ተሰማ በሚል ፍጹም ሰይጣናዊ ቁጭት ተነሳስቶ ጥፋተኛነቱን መካድና በሌሎች ላይ ለመላከክ እንበለ እፍረት "መንደረተኞች" ብሎ ሆያ ሆየ ሲል ተሰምቷል።
ይህም በቀጥታ ስሙን ለሰው አወረሰው ሲሆን ይልቁንም አገራችን ከቶ በምን ዓይነት ስግብግብና ጭፍንፍን ፈላጭ ቆራጭና ዝቃጭ ቅጥረኛ የምትገዛ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል።
የወያኔ ባንዳዎች "ኢትዮጵያዊነት፣ የሕዝቦች እኩልነት" መሠረታዊ መርህ በተግባር የአድዋ ቀበሌ ጥቂት ጉጀሌዎችና በጎሳ ዝምድና ትስስር ያላቸው የኤርትራ ተወላጅ ተባባሪዎቻቸው ብቸኛ ተጠቃሚነትና የበላይነት የሰፈነበት፣ ተለጣፊ ሆድ አደር የጎሣ አባቆሮዎች በሙስና አረንቋ ተዘፍቀው የሚንደላቀቁበትና በአንጻሩ ደግሞ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለከፍተኛ ችጋር፣ ለስደትና የኑሮ ውድነት ተዳርጎ ያለበት ሁኔታ ነው።
ከወታደራዊ ደርግ ውድቀት መልስ ወያኔ ኢሕአዴግ የባንቱስታ አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካን በጠመንዣ አፈሙዝ ጭኖበት ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኸው በፈላጭ ቆራጭ የከፋፍለህ ግዛ ይተራመሳል፣ ይበዘበዛል።



EthioLion.Com
Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

# ፀረ ዐማራ ቅስቀሳ ትናንትና ዛሬ

ወያኔና ሻእቢያን ለሥልጣን ያበቃው ዋና አቀናባሪ የአሜሪካው ስለላ ድርጅት አባ ወራ ይሁዲው ፓውል ኼንዝ በመጋቢት ወር መጨረሻ 1982 ዓ.ም በዋሽንግተን ከተማ ከመለሰ ዜናዊ ጋራ ባደረገው ቃለ ምልልስ የዐማራ የበላይነትን አንቀበልም ስትል ምን ማለትህ ነው? የወያኔ ሠራዊት እያለፈባቸውና እየተደገፈባቸው ያሉት እንደ ላስታ፣ ጋይንት፣ ዐማራ ሳይንት ወዘተረፈ ያሉት አካባቢዎች የዐማራ ሕዝብ የሚኖርባቸው እንደመሆናቸው የናንተን እንቅስቃሴ ይህ ሕዝብ እንዴት ያየዋል? ብሎ ላቀረበለት ጥያቄዎች የሰጠው ምላሽ፤ የእነዚህ አካባቢዎች ዐማራ የተጨቆነ ነው። ስለ ዐምሐራ የበላይነት ስናወራ የምናወራው ስለ ሸዋ ዐማራ የበላይነትና ባለፉት የመቶ ዐመታት ውስጥ አዲስ አበባን ማዕከል አድርጎ ስለተገነባው የበላይነት ነው።

ይህ አመለካከት በቀጥታ የፋሽስት ጣሊያኖች ውጥን እንደሆነ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። "ያማራ ገዥ መደብ፣ ነፍጠኛ ትምክህተኛ" ወዘተረፈ እየተባለ በዐማራው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የጥላቻ ቅስቀሳ ተነዝቷል፣ ይነዛልም።
የሸዋ ዐማራ ገዥ መደብ የሚባለውም የጥላቻ ቅስቀሳው ስልት ነው እንጂ በተጨባጭ ምንም እውነትነት የለውም። ይህንንም ሐቅ እንግሊዛዊው ፕሮፌሰር ክርስቶፈር ክለፎም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ኢኮኖሚ በተሰኘ መጽሐፋቸው ባለፉት 117 ዓመታ ማለትም ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም ወታደራዊ ገዥ ያሉትን ርዕሰ ብሔሮች ብሔረሰባዊ ጥንቅር ሲያብራሩ 44% ኦሮሞ፣ 15% ትግሬ እንደነበሩ ዘግበዋል።
የአጤ ኃይለሥላሴን መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ከነበሩት ግለሰቦች ውስጥ 69% ከሸዋ ቀጥሎም ከኤርትራ ቢሆንም እንኳ ሸዋ ሲባል ማለት ሳይሆን ሸዋ ጅኦግራፊያዊ እንጅ ያንድ ጎሣ ክልል አይደለም። በዛ ያሉ ነገዶች እንደ ዐማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ከምባታ፣ ሃድያ ወዘተረፈ የመሳሰሉት ሰለሚኖሩ ከቅይጥ ቤተሰብ የመነጩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንደነበሩ ተመልክቷል።
ለብዙ ዓመታት በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ አካባቢዎች የሚኖሩት ሠርቶ አደር ሰላማዊ ዐማሮች "የሸዋ ገዥ መደብ" አባል አይደሉም። የጎሣ ፖለቲካ አቀንቃኞች በዐማራ ሕዝብ ላይ ጭፍጨፋና ማፈናቀል በነፍጠኛ ሥርዓት ላይ የሚወስዱት የበቀል ርምጃ አስመስለው ለማቅረብ የሚያደርጉት ዐሪመኔ ድርጊት ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው። ይልቁንም የባላባታዊ ሥርዓት የነበረው የመሬት ስሪት በመላው ኢትዮጵያ ከ1967 ዓም የደርግ የመሬት አዋጅ ወዲህ አክትሟል።
በአዋጁ እንዲያውም ዐማራው ሕዝብ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎና በሸዋ የሺህ ዘመናት የግልና የርስት ስሪቱን ተነጥቆ የመንግሥት ተብዬ ቅጥረኞች ጭሰኛ ተበዝባዥ ሆኖ በቀበሌ ካድሬና የወያኔ ምንደኛ ሰላይ ዘወትር ቁም ስቅሉን ያያል። ቀድሞም ሆነ አሁን በገጠር የሚኖሩት አማራ ገበሬዎች የመሬት ባላባቶች አይደሉም። ከጎንደር ከጎጃም፣ ከወሎ ፍልሰና ተንቀሳቅሶ ለዘመናት የኖረውና የሚኖረውን ገበሬ ነጋዴ፣ ሠራተኛ ወዘተረፈ ላይ በጎሳ ፖለቲካ መመሪያነት፣ በጎሳ ድርጅት ታጣቂዎች ፈጻሚነት በወያኔ አዝማችነት በያለበት የተፈጸመውን ግፍና በደል ከቶ አይዘነጋም።
ያማራ ሠርቶ አደር በሚኖርበት አካባቢ ሁሉ በላቡና ጥረቱ የሚተዳደረውን በወያኔ ሻእቢያ ምልምል የጎሳ ታጣቂ ጠባብ ጎሰኞች ሁሉ በጭፍን ጥላቻ፣ እብሪትና ዘረኝነት ልዩ ዒላማ የሆነው ወያኔና ሻእቢያ በምዕራባውን ርዳታ ድጋፍ ስልጣን ከያዙበት ወዲህ እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዘመን በስተቀር አልተደረገም ነበር።

ይህም ሊሆን የቻለው በወያኔ ሻእቢያ ቅጥረኛ መሪዎች ዘንድ ሥር የሰደደው እይታቸው፣ ኢትዮጵያን ለረጅም ዘመናት ሲገዛ የኖረው ዐማራው ብቻ ነበር ብለው ማመናቸው ነው። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ተልዕኳቸውን ሴራ ዐማራው ፈጽሞ እንደማይቀበላቸው፤ ከሕዝቡ ብዛትና የአሰፋፈር መልካ ምድር ሁኔታ ታላቅ መሰናክል እንደሆነባቸው ተረድተዋል። ስለዚህም ባለፉት ዘመናት ለተከናወኑትን ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂው ዐማራ መሆን አለበት የሚል የረጅም ጊዜ ተረት ተረት ያናፍሳሉ።

የወያኔ ኢሕአዴግ አባላትና ሠራዊታቸው በጠቅላላው የተቀረፀና የተዋቀረው በዚሁ መንፈስ ሲሆን ዐማራው ያለበትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በይበልጥ ማባባስ፣ ለም የርሻ መሬቱን ለውጭና ለትግሬ ጎሣዎች መከለል፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ በማለት እርስ በርሱ ተከፋፍሎ እንዲናቆር፣ በጠባብ የጎሣ ስሜት አጥር ውስጥ ተከልሎ የጠንካራ ኢትዮጵያዊነቱን ብሔራዊ ስሜቱን እንዲተው ለማስደርግ ታስቦ በወያኔ ሳንባ የሚተንፍስ ተለጣፊ የዐማራ ተወላጅ እንኳ ባልሆኑት ተዘጋጅቶ ብአዴን የሚል መጠሪያ የተለጠፈበት ፀረ ዐማራ ቡድን ነው። በመሆኑም ባማራው ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ይነዛል። ይህ የወያኔ ሻዕቢያ ጥርቃሞ ቡድን በተለይም ከዐማራው ክልል ውጪ የሚኖሩትን ዐማራዎች ለይቶ ለከፍተኛ ጥቃትና መፈናቀል ያጋለጠ የወያኔ ሻዕቢያ ቅጥረኛ ቅልብ አስጨፍጭያፊ ነው።

# የጋዜጣው መግለጭያ ታካይ

መለሰ ዜናዊ ከሰጠው ጋዜጣዊ መግላጭያ ላይ ተጨማሪው በሪፖርተር ጋዜጣ ዕለተ እሁድ ሚዚያ 22 ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ.ም <<ጉራፈርዳ ፍሬው ከገለባው ሲለይ>> በሚል ርእስ በአንድ ግለሰብ ስም አምባቸው አዱሱ ተብዬው ያሰፈረውን ይመለከቷል።
(http://www.ethiopianreporter.com/ cmponent/ content/ article/ 303 ...)

ወያኔው በተቀዳሚ የጉራፈርዳን የዐማራ ተወላጅ ስፋሪዎችን ወቅታዊ ሁኔታ ከዘመነ አጤ ምኒልክ የደቡብ፣ የምዕራብና የምሥራቅ ጥንታዊ ኢትዮጵያ ግዛት ማዋህድ ዘመቻ ጋራ በማነፃፀር ያትታል። "የሰሜኑ (አቢሲኒያ) ክርስቲያናዊ ሥርዎ መንግሥት ወደ ማዕከል፣ ደቡብ ምዕራብና ደቡብ ምሥራቅ የአሁኑ የኢትዮጵያ አካባቢዎች መስፋፋትና አካባቢያዊ መንግሥታትን ማስገበሩን....." በማለት ይጀምራል።
ይህ ዓይነቱ ትረካና አብሶም "አቢሲኒያ" እያሉ ማናፋት የጎሳ ነፃ አውጭ ግንባር ተብዬዎች ዝባዝንኪ መሆኑንና ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከምኒልክ ወዲህ እንደተመሠረተችና የተባሉት አካባቢዎች አስቀድሞ የጥንት ኢትዮጵያ ግዛት እንዳልነበሩ ለማስመሰል የሚደረግ አዲስ የፈጠራ ተረት ተረት መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ከ16ኛው ክፍለ ዘመን የወረሞ ጎሳዎች ወረራና መስፋፋት በፊት በጥንታዊው ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ፈጠጋር፣ ወጂ እናሪያ፣ ጋሞ፣ ዳሞት፣ ቢዛንሞ፣ ሸዋ ወዘተረፈ ከነባር ነዋሪዎቹ ሕዝብ ዐማራው አንዱ ነበር።
በታካዩ መግለጭያ ላይ ታሪክ ተፋልሶ የዐማሮች በደቡብና መሃል አገር መሰፈር ከምኒልክ ወዲህ ጀምሮ ብቻ እንደሆነ ተተርኳል። ሐተታውም ሲቀጥል፣

"የአጤው መንግሥት በየካቲት 1966 ዓ.ም አብዮት ተወግዶ ተከታዩ የደርግ ወታደራዊ መንግሥት "የፊውዳል" የመሬት ይዞታ ሥርዓትን በ1967 ዓ.ም ያከተመ ቢሆንም በተለያዩ አካባቢዎች መሬት ይዘውና ሰፍረው የነበሩ ያማራ ተወላጆች በአራሽነት የያዟቸውን መሬቶች ይዘው የቀጠሉብት ሁኔታ ተፈጥሯል።"

በማለት የተተረከው ሃሳብ ቀጥተኛ አባባል ያማራ ተወላጅ ገበሬዎች በሚኖሩበት ቀዬ መኖር አይገባቸውም ነበር። ይህም ማለት የሚያርሱትና የሚኖሩበት መሬት ዓለም ስትፈጥር ጀምሮ የነባር ጎሳ ተብዬዎች ብቻ ልዩ ሃብት ነው። በዚህ ዓይነት አመለካከት በተለይ የኦሮሞ ጠባብ ጎሰኞችና ነፃ አውጭ ግንባር ተብዬዎች ይልቁንም በቀዝቃዛው ጦርነት አፍላ ወቅት የኢትዮጵያ አስተዳዳሪ አጤዎች ይሁኑ ወታደራዊ ደርግ መቶ በመቶ ዐማሮች ብቻ እንደሆኑ ተደርጎ በውጭና በአገር በቀል ምልምል ፀረ ዐማሮች ሰፊ የጥላቻ ዘመቻ ተናፍሷል።

በመቀጠልም <<ከደርግ ውድቀት በኋላ "ኅብረ ብሔራዊ" የፌደራል ሥርዓት በቋንቋ መሠረት ላይ በመዋቀሩ ምክንያት ለዐማራ ተወላጆች እንዳለፈው ጊዜ በቀላቅሉ ወደየ አካባቢው ሄደው ለመስፈርና ለመኖር ሁኔታው አስቸጋሪ አድርጎታል።>> የተሰኘውን እንመልከት።
በኢትዮጵያ ልክ በፋሽስት ጣላያን ወራሪዎች ዕቅድ መሠረት በዓለም ላይ በተለይም በአፍሪቃ አህጉር ልዩ የሆነው የወያኔ የባንቱስታን አፓርታይድ የዘር ወይም የጎሣ ክልል ፌደራሊዝም ተብዬውንና በአንድ አነሰተኛ ጉሣ የበላይነት የሚዘወረውን፣ መላውን ሕዝብ በጠመንዣ



Ethiopia Will Prevail!

EthioLion.com

EthioLion

ኃይል ወድሮ በፍርሃትና ጭንቀት አዘቅት ውስጥ አስገብቶ በሚያኖርበት ፍጹም ኢደሞክራሲያዊና ኢፍትሐዊ የአስተዳደር ሥርዓት "ኅብረ ብሔራዊ" እያሉ ማላዘን ለምዕራባውያን ፀረ ኢትዩጵያ የወያኔ ሞግዚቶች ፍጆታ እንጂ ለኛ ግን አይሠራም።

በርግጥም ያማራ ተወላጆች እንኳን ወደ ሌላው ሄደው ለመስፈር ይቅርና ወያኤ በከለለው የጎሣ እስር ቤት ቁጥር 3 ውስጥ አስተዳዳሪ የሚሆን አማራ እንኳ ጠፍቶ ከፍተኛ ባለሥልጣኖቹና ሹማምንቶች ሁሉ ኤርትራውያንና ትግሬዎች ከመሆናቸውም ሌላ ሕዝቡ በሰላምና በነፃነት እንደማይኖር የተረጋገጠ ነው።
የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በክልሉ ውስጥ ያለውን ዐማራ ሕዝብ ደግሞ ጨቋኝና ተጨቋኝ እያሉ በመከፋፈል ሕዝቡ እጅ ለእጅ ተያይዞ ገንዘቡንና ጉልበቱን በሙሉ ልብ ተማምኖ አስተባብሮ በልማት ተግባር ላይ እንዳይሰማራ የተደርገው ለወያኤ የግል ኩባንያዎችና ከበርቴዎች ጥቅም ማጋበስ ሁኔታውን ለማመቻቸት ታስቦ ነው።
ዐማራ ያልሆኑት የወያኤ ዐማሮችና ሆድ አደር ተለጣፊዎች የሕዝብን ቁጥር ለመቀነስ በታቀደው መወረት በምዕራባውያን ዘረኞች የረቀቀ ስልትና ከፍተኛ የገንዘብና ቁሳቁስ ርዳታና ትብብር "የቤተስብ መምሪያ" መንግሥታዊ ያልሆኑ የርዳታ ድርጅት ተብዬዎች በዐማራው ሕዝብ ላይ ከጎጥ እስከ አውራጃ ባላው ያስተዳደር መዋቅር ውስጥ እንድ አሸን ፈልተው ይርመሰመሳሉ። የኢትዩጵያን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ በተለይም ዐማራውን ለማጥፋት የማይፈነቀል ድንጋይ ከቶ ምን አለ!!
በዓለም አቀፍ ዘረኛ ጽዩናውያን በይሁዲ ሃይማኖት ሽፋን ፈላሻ፣ ክርስቲያንና እስላም ኢትዩጵያውያንና ከጎንደርና ከትግሬ መንደራቸው በዘመናዊ ባርነት ተፈንግለዋል። የጽዩናውያን ባሪያ ፍንገላም ያለማቋረጥ በሰፊው ቀጥሏል። የመለስ ዜናዊ ወያኤ መንግሥት የባሪያ ንግዱን ከአረቦች ጋራ ወግኖ አጧጡፏል።

ሰሞኑን በየወሩ ከ45 ሺህ በላይ ሴት ወጣቶችን ለሳውድ አረቢያ የድንጋይ ዘመን ፊውዳል ለመፈንገል መስማማቱ ታውቋል። ባሪያ አሻሻጩ ሼክ አላሙዲን የጋምቤላንና የመተከልን ለም መሬት በሰፊው ከአገሬው ሕዝብ አስለቅቆ ከያዙት ከወያኤዎች፣ ከሕንድ፣ ከቻይና፣ ኮሪያና ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ ወዘተረፈ ቱጃሮች አንዱ ነው።
ወያኤ ያማራውን እንቅስቃሴ በቅድሚያ መገደቡ ግልጽ ነው። ፋሽስት ጣሊያኖችም ያደረጉት ይህንኑ ነው። ያማራውን ገበሬ ሕዝብ ከደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ በማፈናቀል ያረበኞችን ትግል በመላው ኢትዩጵያ ለማዳከም ታቅዶ ነበር። ግን አልሰራላቸውም።
የወያኤን የባንቱስታን የጎሣ ፌደራሊዝምን ያማራ ልሂቃን ተቃወሙት፣ ይቃወሙታል የተባለው በጣም ትክክል ነው።
ምን መቃወም ብቻ ገና በአፍጢሙ እንደፋዋለን እንጂ። ይህንንም ጠላትም ወዳጅም ማወቅ እንዳለበት አስምረንበታል።
የባንቱስታስን አፓርታይድ የዘር ፖለቲካ በአህጉራችን በደቡብ አፍሪቃ ወደ መቃብር ገብቶ ዲሞክርሲያዊት ደቡብ አፍሪቃ በልጆቿ መስዋዕትነት እንደተመሠረተችው ሁሉ በኢትዩጵያም ምድር እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ስፍና የግለሰብ ነፃነት፣ የሁሉም ነገዶች እኩልነት፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋና ባሕል በተግባር የሚከበርባት፣ የየአካባቢው ሕዝብ የራሱን የውስጥ አስተዳደር ተረክቦ የአካባቢውን አስተዳዳሪዎች፣ የማዕከላዊ መንግሥትን ባለሥልጣናትን በነፃ የሚመርጥበትና የሚሽርበት ያልተገደበ የሕዝብ የሕዝብ ሥልጣንና መብት የሚቀዳጅበትን ሥርዓት፣ የሀገሪቱን አንድነትና ልዑላዊነት አስከብሮ ለጋራ ልማት፣ ክብርና ጥንካሬ ተግባራዊ ማድረግ ዓላማና ግባችን ነው።
በጎሣው የዘር ፖለቲካ መርህ ምክንያት በ"ኦሮሚያ ክልል" የዐማራ ተወላጆች ፍልሰው ለመስፈር አልቻሉም የተባለውም ትክክል ነው። አዎ! በዘመነ ወያኤ ኢሕአዴግ እንዴት ሆኖ ነው በዚያ መስፈር የሚፈቀድላቸው? ወያኤ ኢሕአዴግና ሻእቢያ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በሰኔው ወር 1983 ዓም እነሱ በመርጧቸው ጥቂት ተሳታፊዎች ብቻ የተደረገው ጉባዔ ኤርትራን ለማስገንጠል በቀሪው አገር ላይም የጎሣ ፖለቲካ ለማስፈን የተዘጋጀው "ቻርተር" በውጭ ኃይሎች አስተባባሪነት በሻእቢያ፣ በሕወሀትና በኦነግ ስምምነት የተነደፈ ነበር።
ከጠቅላላው የኢትዩ፡ጵያ ሕዝብ እስከ 45 በመቶ እጅ የሚሆነውን በታሪክ አጋጣሚ በብሔራዊ ግዴታና በማኅበራዊ ኑሮ አስገዳጅነት በሁሉም ክፍለ ሀገራት ከሌላው ነገድ ጋራ ተፋቅሮ፣ ተጋብቶ፣ ተዋልዶና ተዋህዶ በኢትዩጵያዊነት አምኖ የሚኖረው ዐማራ ሕዝብ በሽግግሩ መንግሥት ይሁን በተውካዩች ምክር ቤት ተብዬው ውስጥ አንድም እንኳ ወንበር አልነበረውም። ይባስ ብሎም በያለበት ለታጠቁ የጎሣ ድርጅቶች ተዳርጎ ሲጨፈጨፍ፣ ሃብት ንብረቱ ሲዘረፍ፣ ተወልዶ ታድገበት ቀዬ ሲፈናቀል ቆይቷል። ዐማሮች በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በአሩሲ፣ በወለጋ ወዘተረፈ ከነባር ይዞታቸው እየተፈናቀሉ አገራችሁ አባይ ማዶ ነው ወደዚያ ሂዱ ይባላሉ። በብዙ ከተሞችና ገጠሮች በቁጥር ብዛት ቢበልጡም እንኳ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ መብትየለሽ "መጤዎች" ናቸው። እዚህ ላይ በቅድሚያ "ኦሮሚያ" የተሰኘው የፈጠራ ክልል መሆኑንና እንዴትና መቼ በማን በማን እንደተከለለ በግልጽ ማሳወቅ ተገቢ ነው።
እራሱን የኦሮሞ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግንባር ባይ (ኦነግ) ዛሬ በኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ የኦሮሞ ልዩ ልዩ ጎሣዎች ሰፍረው የሚገኙበትን አካባቢ ሁሉ ከጥንቱ ጀምሮ የኦሮሞ ክልል እንደነበረና ያበሻ ንጉሥ አፄ ምኒልክ ከዛሬ 120 ዓመታት ገዳማ በመውረር በቅኝ ግዛትነት ይዘዋል እያለ ይለፍፋል። ኦሮሞዎች የሰፈሩበትን አካባቢ ሁሉ ከኢትዩጵያ ገንጥሎ ራሱን የቻለ ሀገር መመሥረት አለበት ይላል። ለዚህም እንዲያመቸው ከኢትዩጵያ የቆዳ ስፋት ሦስት አራተኛውን በመከለል "ኦሮሚያ" የሚል ሲያሜ አውጥቷል። ለምስረታው ስኬታማነት ኦሮሞ ያልሆኑ ነዋሪዎችን ከአካባቢው እንዲወጡ በኃይል ማስፈራራትና ማባረር ሲሆን በተለይም ዐማራውን ወገን ለይቶ ግድያና ዝርፊያ አስፈጽሚል። በሌላ በኩልም የአካባቢውን ጥንታዊ ኢትዩጵያዊነት የሚያሳዩትን በተለይም ከዛሬ 400 ዓመታት በፊት ተመሥርተው የነበሩትንና የሚገኙትን የታሪክ ቅርሶችን ማጥፋትና ማውድም ለውሸትና ለፈጠራ ታሪኩ ተቀባይነት ይሆንልኛል ብሎ የጠባብ ጎሰኛው ቡድን ደፋ ቀና ይላል።

ዳሩ ግን ኢትዮጵያ ጥንታዊት አገር በመሆኗ ታሪኳ በራሷ ልጆችና በውጭ ሰዎችም በሰፊው ተመዝግቧል።
የኦነግን ተረት ተረት ውድቅ የሚያደርጉት ሁለት ቁልፍ ማስረጃዎችን ብቻ ማቅረብ ይበቃል።

፩ኛ የጋሞ ተወላጅ የብርብር ማርያም ድብር መለኩሴ የሆኑት አባ ባሕርይ በ1593 ዓ.ም በግእዝ የፃፉት ዜናሁ ለጋላ ማለትም የጋላ ታሪክ በዚያው ዘመን አጠራር ጋሎች በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን ከደቡብ ባሌ ጠረፍ ማዶ በመነሳት ኢትዮጵያን መውረራቸውን በዝርዝር መዝግበውታል። በዚህም መሠረት ባሕርይ ሰለ ጋሎች ንጉሣዊ ያልሆነ የገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመት በሚመረጠው ሉባ እንደሚተዳደሩ፣ የሉባ ደፋጣ ውጊያ ስልትና አጠቃላይ የጎሳውን ባሕል ገልጸዋል።
ባሌን መውረር የጀመረው ቀዳማዊ ሉባ ሜልባህ የተባለው አዝማች ነው። እሱም እ.ኢ.አ 1522 1530 የገላናን ወንዝ ተሻግሮ ባሊን የወረረው። ሁለተኛው ሉባ ሙዳና (1530-1538) የተባለው የጀበና ልጅ ሲሆን የዋቢን ወንዝ ተሻግሮ የወረረው እርሱ ነው። ሦስተኛው ሉባ ደግሞ ኪሎሌ (1538-1546) የተሰኘው የደዋሮ ቆላማ ስፍራ ስሙ አዳል መብረቅ በሚባለው ላይ ወረራ አካሂዷል። ጥንት ደዋሮ የሚባለው አገር ዛሬ ጨርጨርና አዳልና ጋራ ጉራቻ፣ ሐብሮንና ወበራ የሰሜን ምዕራብ ሐረርጌ አውራጃዎችን ያጠቃልላል። አራተኛው ሉባ ቢፎሌ (1546-1554) ሲባል እሱም ደዋሮን በጠቅላላው አወደመ። በፈጠጋርም ላይ ለመዝመት ወጠነ። ነዋሪዎችን ሁሉ ማርኮ ባሪያ አድርጎ <u>ገባሮ</u> በሚል ስም ጠራቸው። አምስተኛው ሉባ ምስሌ ወይም ምችሌ (1554-1562) ይባላል። እሱ ነው ዣን አሞራን የገደለው፤ ከሐመልማል ጋራ ደጎ ላይ የተዋጋው። ሁሉንም አገሮች አውድሞ ከብቱን ይዞ በቋሚነት ሰፈረባቸው። ከዚህ ቀደም ጋላ ይወር የነበረው ከዋቢ ማዶ በመነሳት ተመላልሶ ነበር።
እነዚህን ወራሪዎች ንጉሥ አጥናፍ ሰገድ <u>በአሳ ዘነበ</u> (ማለትም ደዋሮ ውስጥ) ወጋቸው። ኑር ያደረገውን አድርጎ ወደ አገሩ ሲመለስ በአዘሉ ኮረብታ (የይፋት በርሃ ረጅም ተራራ የመናኞች እንደ አሰቦት ገዳም መኖሪያ) አጠገብ ተጋጥመው ዕልቆ መስፈርት የሌለው ወራሪ ጦር ተገደለ። አምስተ- ሉባዎች ለ40 ዓመታት ከገዙ በኋላ የሚልብህ ልጆች ተገረዙና ሐርሙፋ የሚል ስም ወጣላቸው። ሐርሙፋ ነው ጊዮርጊስ ኃይሌን በቀጨኞ የገደለው። እሱም ነው ገኝን፣ አንጎትንና ዐማራን ያወደመና በበጌምድር ላይም ጦርነት የጀመረው። የሙዳና ልጅ ሮቤል ተተካ። እሱም ሸዋን የመዘበረው፣ በጎጃም ላይም ጦርነት የከፈተው። ንጉሥ ነገሥቱ ማለትም አጤ ሠርፅ ድንግል በዝዋይ አካባቢ ተዋግቶ ብዙዎቹን የገደላቸው። የቦረን ወገን ቢርመጂ (1590-1598) ዳሞትን ከቦ ሰውን ሁሉ ማረከ ከብቱን ዘረፈ። ከከብት ቆዳ ጋሻ ሠርቶ የሚያን ምርጥ ቀስተኞችን ተከላከላቸው። ቀጥሎም የቢፎሌ ልጅ ሙለታ (1598-1606) ተሾሞ በጎጃም ላይ ዱላጎን አደረገ። ዱላጎን ማለት የጉትያ ማለትም የዘረፋ ወረራ ነው። ሙለታ የራስ ወለድ ክርስቶስን አገር ወረር። ነገር ግን ራስ ወልድ ክርስቶስ ሙለታን አሸንፎ የማረከውን ከብት ሁሉ አስመለሰ፣ አጤው አስኪመለስ ድረስ ተከለክሎ አገሩን ለጠበቀው ጀግና ንጉሡ የአገሩ ዋና መኮንን አደረገው። በሙለታ ሉባ ዘመን ነው ሸዋና ዳሞት ምድረበዳ የሆኑት።
፪ኛ የኦነግ "ኦሮሚያ" በአጼ ምኒልክ በቅኝ ግዛትነት የመያዝ ተረትን አፈር ድቤ የሚያስገባው ታሪካዊ ማስረጃ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን ወረው ከመስፈራቸው በፊት ወደ ሀገራችን ከመጡት የዘመኑ ያውሮፓ ኃያል መንግሥት የፖርቱጋል 3 መልክተኞች ለስድስት ዓመታት ያህል ከ1520 እስከ 1526 ዓ.ም ቆይተው ከተመለሱት አንዱ ፍራንሲስኮ አልቫሬስ በአዘጋጀው መጽሐፍ ላይ በወቅቱ የነበረውን የኢትዮጵያን ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ግዛት የሚያሳይ ካርታ ተስሏል። አባሪውን ካራ ይመልከቷል።



Ethiopia Will Prevail!

ሌላው ሐተታ በደቡብና በጋምቤላ ክልሎች የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ዐማርኛ በመሆኑ ምክንያት ዐማሮች **ወያኔ ከልሎ** ከሰጣቸው ውጪ እየፈለሱ ለምሳሌ እንደ ጉራፈርዳ በብዛት መስፈር ችለዋል። በዚህ ቦታ ሰፋሪዎችን የሚጠይቃቸው ማንም የለም። ቢጠየቁም እንኳ ባዶ መሬት ነው እያሉ ደኑን ይመነጥሩታል የተባለውን ያጤኗል።

ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው አንደኛ ወያኔ በደቡብና ሌሎች አካባባቢዎች ያማርኛን ቋንቋ መጠቀመቸው እንዲያቆሙ በመቀስቀስ ላይ መሆኑን ነው። ይልቁንም ያማራውን ሕዝብ ከደቡብ ወገኖቹ ጋራ ለማቃቃር የወያኔው ታካይ መግለጭያ የሚከተለውን ይዟል፣

<<የሕዝቡን እንግዳ ተቀባይነት እንደ ሞኝነት በመቁጠር (ደቡብ የዋህ ነው) >> በማለት ቀርቧል።

አዎ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ደጉና ኩሩው ኢትዮጵያዊነቱን ከደርግ ውድቀት በኋላ በዘመነ ወያኔ በዴሞክራሲ ሽፋን ያንድ ብሔር የበላይነትና የጎሣን ፖለቲካ በአፅንኦት ከሚታገሉት ግንባር ቀደም ነው።
ከዐማራ ክልል ጨምሮ ከተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች በተደራጀ ሁኔታ ወደ አካባቢው አየፈለሱ ደኖችን በመመንጠር ኖረዋል የተባለው ፍጹም ውሸት ነው። በመጀመሪያ በቅርብ ዘመናት ውስጥ በጉራፈርዳ የሰፈሩትና ዛሬ በወያኔ ትዕዛዝ በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ የክልሉ ፕሬዘዳት አስፈጻሚነት የተፈናቀሉትና የሚፈናቀሉት ያማራ ሰፋሪዎች ነባሩ ሕዝብ በይፋ ማስታወቂያ ጋብዟቸው ክፍት ሣራማ የሆነውን መሬት በሕጋዊ መንገድ አከፋፍሎ በመስጠት ከገበሬዎቹም በይዞታቸው መጠን ግብር ሲሰብሰብ የቆይ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።
ገበሬዎቹ ይህን በትክክል ለመፈጸማቸው የያዙት ሕጋዊ ሰነድ በእጃቸው ይገኛል።

"ጭለማን ተገን አድርገው ለደን ልማት፣ <u>ለኢንቨስትመንት</u> እንዲሁም ለሕዝቦች ማኅበርሰባዊ ሥርዓቶች ማካሄጃ የተቀመጡ መሬቶችን የሚወሩና ዛፎችን የሚመነጥሩ ግልሰቦችን በሕገ ወጥ መንገድ ከያዙት መሬት ማስለቀቅ ነው" የተባለው ፈጽሞ ያልሆነ የፈጠራ ወሬ ነው።
ለኢንቨስትመንት እየተባለ ነባሩ ሕዝብ በያለብት መፈናቀሉ ሐቅ ነው። ከትግሬ በስተቀር በሌሎች ክልሎች ለም የርሻ መሬት መቀራመት ሁኔታን መላው ዓለም አውቆታል። በኢትዩጵያ የክልል የሥራ ቋንቋ ዐማርኛ መሆን እንዴት ሆኖ ነው ለዐማራ ሰፋሪዎች የተለየ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለው? ያማራ ገበሬዎች መቼም የክልል አስተዳደር ቢሮ ሠራተኞ አይደሉም።
በሁለተኛ ደረጃ ወያኔውን እጅግ በጣም እርር ብግን ያስደረገው መለስም ብግልጽ እንደተናገረው በጉራፈርዳ ወረዳ ብዙ ዐማሮች **በአንድነት ሰፍረው** መገኘታቸውና መኖራቸው ነው። በመሆኑም ነው ጉራፈርዳ **ምሥራቅ ጎጃም** ሆነች ብሎ የወሻከተው።
በርግጥም ሰፋሪዎቹ የመጡት ከተለያዩ አካባቢዎች እንጂ ከምሥራቅ ጎጃም እንደልሆነ ተፈናቃዮቹ ሲጠየቁ
ተናግረዋል። ታዲያ! ጉራፈርዳ ምሥራቅ ጎጃም ሆነች ብሎ ማወናብድ አንድም ሥር የሰደደ ያማራ ጥላቻ የአእምሮ መቃወስ በሽታ ነው።
አለበዚያም ደግሞ እነዚህ ታታሪ ገበሬዎች ራሳቸውን ችለው መኖር ለአሜሪካንና አውሮፓ ገብሬዎች በኢትዮጵያ የርሃብና ድርቅ ርዳታ ሽፋን ሸቀጥ ማራገፊያነትና የዘወትር ልመና ጥገኛነት ለወያኔና ጀሌ ካድሬዎቹ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት ነው።
አርሶ አደር ገበሬዎችና የአፋር ከብት አርቢዎችን በያለበት የሚፈናቀሉት፣ በጋምቤላ በጣም ለምና ደንግማውን መሬት ለሕንድና ለአረብ

ቱጃሮች በርካሽ የሚቸበቸበው የወያኔዎችን የግል ኪሳ ለመሙላትና በውጪ ባንክ ለሚያከማቹት የገቢ ምንጭ ነው።

**ትግሉ ይቀጥላል!!**
**የባንቱስታን የጎሳ ፖለቲካ ይወገዳል!**
**ኢትዩጵያ በልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ትኖራለች!!**

**ግራዋ ሳሙኤል**
**ገብሬ ጉልቱ**

EthioLion.Com